

# አመራር

ዝግጅት፡ ዑስማን ኑሪ ቶፕባሽ

ትርጉም፡  አብዱልጀሊል ዓሊ ካሣ

# አመራር

ዝግጅት፡ ዑስማን ኑሪ ቶፕባሽ

ትርጉም፡ አብዱልጀሊል ዓሊ ካሣ

## መቅድም

እጅግ አዛኝና ሩህሩህ በሆነው በአላህ ስም

ዓለማችን በቁሳዊ አመራር እና ሥልጠና ከጣሪያ የደረሰችበት ዘመን ነው፡፡ አብያተ-መጽሃፍት በአመራር ነክ ዙሪያ በሚያጠነጥኑ መጻህፍት መሞላት ይዘዋል፤ “ማኔጅመንት እና ሊደርርሽፕ” በሥርዓተ-ትምህርት ውሥጥ ተካተው እንደ ሣይንስ መጠናት ከያዙ ሰነባብተዋል፡፡ በአመራር ዙሪያ የሚሰሩ ተቋማት በዓለማችን ጉያዎች ተሰግስገዋል፤ ዓለማችን ተሰባስባ በ”ግሎባላይዜሽን” መንደር ከከተሞች ከራረሞች፤ በሉላችን ሕብረ-ሀገራት የተደራጁ ሉላዊ አስተዳደሮች መመራትም ከጀመረች እንሆ አንድ ክ/ዘመንን ልታስቆጥር ነው፡፡ ግና ከዚህ ሁሉ ግስጋሴ በኋላም ዓለማችን በአመራር ጠኔ ተሽመድምዳለች፤ ፈርዖኖች ዙፋኖቿን አጣበዋል፤ ነዋሪዎቿ የኸጧብን ልጅ የተመኙበት ዘመን መሆኑን በማህተመ ጋንዲ አፍ በኩል ሥሞታ ቢያሰሙም በእጅ አዙር ባርነት ውሥጥ ይኖሩ ዘንድ ፈርዖኖቹ አልፈቀዱም፤ ሞትና ፈንጅ የዶሮ ጩኸት ሆኖ ንጋቱን የሚያበስርበት ዘመን፤ የሰይጣንን ዘመን ለማንበር የእውነትን ጥላ የተከተሉ ሁሉ እንደ ቁረይሽ ጨቅላ እንስቶች ከነህይዎታቸው የሚቀበሩበት ዘመን፤ የአመራርና አስተዳደር ተቋማት የኢብሊስን ፕሮጀክት የሚያስፈጽሙበት ጊዜ!

ዓለማችን የሰይጣን መማክርት ያሏቸው መሪዎች ሳይሆን ሰይጣናት የሚፈሩት እንደ ዑመር ኣይነት መሪዎች ያስፈልጓታል፡፡ የሰው ዘሮችን ወደ ተፈጥሯቸው ግብ የሚያደርሱ አመራሮች ያስፈልጓታል፡፡ ኢስላም የሰው ልጆች ከፍተኛ መሻሻልንና ምሉዕ ሥልጧኔን መጎናጸፍ የሚችሉት በሕብረተሰባዊነት (በዑማነት) እንደሆነ ይገልፃል (ቁርዓን ምዕራፍ 3፡ ቁጥር 104-110)፤ ህዝቦች በጎና ትክክለኛ መሪዎቻቸውን እንዲያከብሩና እንዲከተሉ ( ም4፡ ቁ 59)፣ አመራሮቹም ተመሪዎቻቸውን እንዲያመካክሩና ከህዝቦቻቸው ግብአት እንዲወስዱ (ም42፡38) የመሳሰሉ የሥነ-አመራር መርሆችን አላህ አስቀምጦልናል፡፡ አመራርነት በኢስላም አማና (አደራ) ነው፡፡ እያንዳንዱ የህብረተሰብ አባልም በድርሻው እርኛ ነው፡፡ ኃላፊነት አለበት፤ የመምራት፣ የመመራት፣ መሪዎቹን የማስተካከል፤ በሚመራቸው ላይ ፍትሃዊና ቅን የመሆን አማናን የተሸከመ እርኛ ነው፡፡ አላህ ለኣዳም የዚህች ምድር አምባሳደርነት ኃላፊነትን አሸክሞታል ይህ አማና የመምራትና የማስተዳደር አማና ነው፡፡ ከጉንዳን እስከ ታላቋ ምድር ድረስ ለሰው ልጅ በአደራ የተሰጡ አማናዎች ናቸው፤ የዱር እንስሳቱ ማደሪያቸው የተጠበቀ፣ ደህንነታቸው የታመነበት ይሆን ዘንድ ነበር አምባሳደርነቱ ግና ዘረ-አዳም ለራሡም አልሆነ፡፡ በኮረኮንች መንገድ እግሯ እንዳይደናቀፍ ለበቅሎ መንገድ የሚያሰራ መሪን ደፍጥጦ በ “Serevival of the fittest” መርህ ሳቢያ የቄሳርን ዘገር ነቅናቂ፣ የፈርዖንን “ወንድ ልጅ ለካራ” መርህ አንባሪያን አመራሮችንና ሥርዓታቸውን ይሁንታ የቸረ ትውልድ ሆኗል፡፡ ቱርካዊው ዑስማን ኑሪ ቶፐባሽ ለዚህ ግራ መጋባት ቁልፍ ያለውን የአራቱን ምርጥ ኸሊፋዎች አመራር ሞዴል የሚያስቃኝ `Principles from the lives of the Four Rightly-Guided Caliphs` የተሰኘ መጽሀፍ ደርሶ እንካችሁ ብሏል፡፡ እኔም አላህ ፈቅዶልኝ መጽሀፉን ሳነብ ያገኘሁት ቁም ነገር ቢበዛብኝ ስለምን ወዳጆቼንስ አላቃምሳቸውም ስል ከመጽሀፉ ውሥጥ “On Society and Rulers” የተሰኘችውን የመጽሀፉን መቋጫ ምዕራፍ ወደ አማርኛ “አመራር!” በሚል ርዕሥ መልሻታለሁ፡፡ ዑስማን ኑሪ ቶፐባሽ **“ጠምዛዛ ነገር ጠምዛዛ ጥላ ይኖረዋል፡፡”** የሚለውን የዓሊይን ምርጥ ንግግር በዚህች ሥራው አስረድቷል፡፡

የትርጉም ሥራ በርግጥ የመጀመሪያዮ በመሆኑ አያሌ ግድፈቶች እንደሚኖሩባት ተስፋ አደርጋለሁ፤ አመል ሆኖብኝ የማስፋት፣ የማርዘም አባዜዮ አልላቀቀም ብሎኝ ትርጉሙን በልቅ የትርጉም ዘዴ ለጥጬና ግላዊ አረዳዴን ጭምር በማካተት ወደ አማርኛ ለመመለስ ሞክሬያለሁ፡፡ የፍሬ ሰው ይበላችሁና ፍሬዋን እንጅ ገለባዋንስ አንጓላችሁ አንፍሱልኝ! መልካም ነገር ካገኛችሁ ከአላህና ከመልዕክተኛው (ሡ.ዐ.ወ) ነው፤ የተቀረው ከደራሲው፣ ከእኔና ከሸይጧን ነውና አላህ ይመራን ዘንድ ዱዓችሁ አይለየን፡፡ አንባቢያን ከላይ የተጠቀሰውን ሙሉ መጽሀፍ ያነቡ ዘንድ እየመከርኩ አላህ የሰከነና እውነተኛ አመራርና ህዝብን በአለማችን ላይ እውን ያደርግ ዘንድ እንማጸነዋለን፣ በአወቅነው ከሚጠቀሙት ሰዎች አላህ ይበለን፡፡

አሚን

አብዱልጀሊል ዓሊ ካሣ (አቡ አሙተል መሊክ ኢብን አሙተልመሊክ)

መስከረም 2008 ዓ.ል

## ህዝብና መሪዎቹ

ፍጥረታቱ ካላቸው ተክለ ቁመና አንጻር የሚገባቸውንና በልካቸው የተሰፋውን ማህበረሰባዊ የህይዎት አመራር ቅርጽ አላህ (ሱ.ወ) ያድላቸዋል፡፡ አላህ (ሱሳ) የሰው ዘሮችን በቁሳዊውና በመንፈሳዊ ቁንጅና ውበት ያጌጡ ዘንድ ፍላጎቱ ነው፤ ከሁሉም እይታ የተስማማና የተጣጣመ የረጋ ህይዎትም ይኖሩ ዘንድ ይሻል፤ ይህም በተከበረና በላቁ ሁኔታ ላይ ስለፈጠራቸው ነው፡፡ ቁርአን እንዲህ ይላል፡

***"ሰማይንም ከፍ አደረጋት፡፡ ሚዛኑንም አሰቀመጠ፡፡ ሚዛን ላይ አትበድሉ፡፡" (አል ረሕማን፡ 7-8)***

ሌሎች ፍጥረታቶች እርስ በእርሳቸው ካላቸው የተሳሰቦትና የመደጋገፍ ባህሪ አንጻር አላህ (ሱ.ወ) የአዳም ዘሮችን እርስ በእርሳቸው እጅግ ተደጋጋፊና ጥገኛ አድርጎ ነው የፈጠራቸው፡፡ የሰው ልጆች በማህበረሰባዊነት፣ በጎሳ በብሄር እና በግዛት ለመኖር ተፈጥሯዊ ዝንባሌ አላቸው፡፡ የገለልተኝነትን ህይዎት የሚመርጥ የለምና፡፡ ይህን ተፈጥሯዊ ዝንባሌ በተጣጣመ ሁናቴ ለመምራት ማህበረሰብን በጥበብ የሚመራ መሪ፣ በተመሪዎችና በመሪ መካከል የሚኖረውን የግንኙነት ሚዛን የሚሞሉ አመራሮች ይኖሩ ዘንድ ግድ ይላል፡፡

አንድ ማህበረሰብ በጥበብ በሰከነ ጊዜ የዚያ ማኅበረሰብ መሪና ተመሪዎች እርስ በእርሳቸው አንዱ የሌላኛውን ቅርጽና ምስል የሚያሳዩ ሆነው ይገኛሉ፡፡ ስለዚህም ነው የተደራጁና የገዘፉ ታላላቅ ግዛቶችም ሆኑ የድኩማን ትናንሽ ግዛት ህዝቦች የመሪዎቻቸውን አካላዊ እና ስነ-ልቦናዊ ተክለ ቁመናን ይዘው የሚገኙት፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም መሪዎች እንደ ግለሰብ የዚያን ማህበረሰብ ገፅታ ይዘው ያድጋሉ፡፡ አመራሮች በደግነትና በክህሎት በተካኑ ጊዜ ህዝቦቻቸው በደህንነትና ሰላም ይበለጽጋሉ፡፡ መሪዎች ይህ በተሳናቸው ጊዜ ደግሞ በተቃራኒው ህዝቦቻቸው በቁሳዊና ማህበረሰባዊ ቀውስ ውስጥ እንዲዳክሩ ይሆናል፡፡ በተጓዳኝ ሁኔታ ደግሞ ማኅበረሰብ ሁለንተናዊ መሻሻል ሲያደርግ ትክክለኛ መሪዎችን ያፈራል፡፡ ህዝብ እንደ ህዝብ የሞራል እሴቶችን ጥሶ በክሽፈት ርቆ በተገኘ ጊዜ ግና ራስ ወዳድ አመራሮች ይነግሳሉ፤ የሰከኑ ብልህ አመራሮችን የሚያበቅል ዘር ይታጣል፤ መሪዎች የማህበረሰቡ ሁለንተናዊ ማህበራዊ ነባራዊ ሁኔታ ፍሬ ናቸውና፡፡

የአንድ ማህበረሰብ ተጨባጭ ሁኔታዎች በታወኩና በተበላሹ ወቅት መሪዎችና ተመሪዎች ለውድቀታቸው ኃላፊነትን ሊወስዱ ይገባል፤ ይህም እያንዳንዱ ወገን የየድርሻውን መዝዞ ራስን በማሻሻል የሚጀምር መሆን ይኖርበታል፡፡ የሌሎችን ባህሪ በመታገስና በመቀበል ሂደት ውስጥ የራስን ባህሪና ስብእና በቅርበትና በጽሞና ማጥናትና መገምገም ተቀዳሚው የኢስላማዊው ፍኖት መርህ ነው፡፡ ይህ አካሄድ ለግለሰባዊ እድገትና ምጥቀት ብቻ ሳይሆን ለማህበረሰባዊ ግንባታም ዋጋና ረብ ያለው ነው፡፡ አሏሁ ተዓላም በቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

**" … አላህ በሕዝቦች ዘንድ ያለውን ጸጋ በነፍሶቻቸው ያለውን (ኹኔታ) እስከሚለውጡ ድረስ አይለውጥም…"** (አል-ረዕድ፡11)

እንዲሁም በአንፋል ምዕራፍ አያህ ቁጥር 53 ላይ እንዲህ ይላል፡-

**" ይህ (ቅጣት) አላህ በሕዝቦች ላይ የለገሰውን ጸጋ በነፍሶቻቸው ያለውን ነገር እስከሚለውጡ ድረስ የማይለውጥ በመኾኑ ምክንያት ነው፡፡ አላህም ሰሚ ዐዋቂ ነው፡፡"** (አል-አንፋል፡53)

ከላይ በቁርአኑ አያዎች[1] በግልጽ እንደተመለከተው አንድ ማኅበረሰብ ከፈጣሪው የተቸራቸው ጸጋዎች፣ ርህራሄና ቡራኬ ሁኔታ ያ ማኅበረሰብ በትክክለኛውና ቀጥተኛው ፍኖት ላይ በሚኖረው ጽናታዊ ቅድመ ሁኔታ ላይ የተንጠለጠለ ነው፡፡ አንድ ማኅበረሰብ የአላህን ችሮታዎችና ጸጋዎች በዘነጋና በካደ ጊዜ የፈጣሪ ችሮታዎችና እዝነት ይርቁታል፡፡ ለዚህም ነው የአላህ መልዕክተኛው ***"በዚያ ሁኔታ ላይ ከመሬት በላይ ከመዋል ይልቅ ከመሬት በታች መገኘት ይሻላል፡፡"*** ያሉት፡፡

በሰናይ ማኅበረሰብ ውስጥ እና በቅን መሪዎች አመራር ስር ለመኖር ከፈለግን የየራሳችንን ግላዊ ህይዎት አላህን በሚያስደስት ሁኔታ ላይ ልንኖር ይገባል፡፡ ስለዚህም ነው ነቢዩም በአንድ አጋጣሚ **"ህዝቦች እንደሚገባቸው ይመራሉ (ይገዛሉ)"**[2] ሲሉ ያስጠነቀቁት ፡፡ የሚከተለው ታሪክም ይህን ነባራዊ ጭብጥ ያሳየናል፡፡

ኢብኑ ሙልጅም በተሰኘ ጠርዘኛ ዓሊይ (ረ.ዐ) በስለት በተወጉ ጊዜ ሰዎች ተረባርበው ደገፏቸው፤ ከፊሎቹም የዓሊይ እስትንፋስ ከመቋረጡ በፊት መሪያቸውን ይሾሙላቸው ዘንድ አበክረው ይጠይቋቸው ጀመር፤ ዓሊይ ግን እንዲህ ሲሉ መለሱ፡- *«የአላህ መልዕክተኛው (ሠ.ዐ.ወ) እኛን በተውብን ሁኔታ ላይ እኔም እተዋችኋለሁ፡፡ እናንተ ዛሬ የጠየቃችሁትን እኛም ነቢዩ ከማለፋቸው በፊት ጠይቀን ነበር፤ የነቢዩ ምላሽም " በእናንተ ውሥጥ መልካምነትን አላህ ከተመለከተ ሰናይ መሪን ይሰጣችኋል፡፡" የሚል ነበር፡፡ እናም አላህም አቡበክርን (ረ.ዐ) የመሰለ ሰናይ መሪ ሰጠን ይህም በኛ ላይ መልካምን አላህ በመመልከቱ ነው፡፡»*[3]

በእርግጥ በርካታ ፈታኝ ሁኔታዎች በዓሊይ የአመራር ዘመን ተከስተዋል፡፡በአንድ ወቅት በዚህ ጉዳይ ላይ፡ "የምዕምናን መሪ ሆይ! ከእርሰዎ በፊት በነበሩ ኸሊፋዎች ዘመን ከተፈጠረ ፈተና በላይ ስለምን በእርሰዎ የኸሊፋነት ዘመን ተፈጠረ?" ተብለው በተጠየቁ ጊዜ የዓሊይ መልስ " እንደኔ ላሉ ህዝቦች በአመራርነት አገለገሉን፤ እኔ ግን ለእንደናንተ ላሉ ህዝቦች በመሪነት በማገልገሌ ነው፡፡" የሚል ነበር፡፡

ዓሊይ ይህን ብለው ሲመልሱ መሪዎች የሚያስተዳድሩት እንደ ተመሪዎቻቸው የሰብዕና ጥራት ነው፡፡ እንደዚሁም ሁሉ የተመሪዎችም የመመራት ብቃትና ድርጊትም በመሪዎቹ ማንነት ላይ የተገነባ ነው፡፡ ዑመሩል ፋሩቅ (ረ.ዐ) በዚህ ጉዳይ አስመልክተው ሲናገሩ " ህዝቦች የመሪዎቻቸውን ዱካና ባህሪ ይከተላሉ፡፡ መሪዎች የእውነትና ቀጥተኛውን መነገድ በተመሩ ጊዜ ህዝቦቻቸውም ቀጥተኛውን መንገድ ይከተላሉ፡፡"[4]

ህዝቦች መሪዎቻቸውን የመከተልና መሪዎቻቸውን እንደ ተምሳሌት የመያዝ ባህሪ አላቸው፡፡ ታሪክም የሚያስረዳን ይህንን ነው፡፡ የኡመያዊው አስተዳደር ኸሊፋ የነበረው ወሊድ ኢብን አብዱልመሊክ ግርማ ሞገሳቸው ያማሩ ንጉሳዊ ህንጻዎችን ይወድ ነበር፡፡በዚያ ወቅት በአስተዳደሩ ሥር ያሉ ህዝቦችም የእርሱን ፈለግ ተከትለው ለአማሩ ህንጻዎች ትልቅ ግምት አሳድረዋል፡፡ በእያንዳንዱ የህይዎት ዑደትና ስብስቦች ውሥጥ የአማሩ ህንፃዎች በህዝቦቹም ዘንድ አቢይ አጀንዳ ሆነው ነበር፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የዚሁ ስርዎ መንግስት ኸሊፋ የነበረው ሡለይማን ኢብኑ አብዱልመሊክ የቅንጦት ምግቦችና መጠጦችን ይወድ ነበር፡፡ በዚያ ወቅት የነበሩ ህዝቦች ዋና አጀንዳም ያው የቅንጦት ምግብና መጠጥ ነበር፡፡

---

[1] አንቀፆች
[2] አል-ሱዩጢ፣ አል-ጃሚአል ሶጊር፣ ቅጽ 2 ገጽ 82
[3] አል-ሃኪም፣ ቅጽ 3፣ 156/4698
[4] ኢብነል ጀውዚ፣ አል መናቂብ፣ ገጽ 223

በዚያው የዑመያ አስተደዳር ዘመን አንድ ቅንና ትጉ መሪ ተፈጥሮ ነበር ይህ ዑመያዊ ኸሊፋ ዑመር ኢብኑ አብዱልዐዚዝ ነበር፡፡ በዑመር የአመራር ዘመን የተገኙ ህዝቦች ለታማኝነትና ፍቅር ትልቅ ግምት የነበራቸው ነበሩ፤የእለት ተዕለት የውይይት አጀንዳቸው ሶላት ነበር፣ በአዕመሯቸው ቀርጸው ስላስቀሯቸው የቁርአን አያዎችና ምዕራፎች ብዛት እያነሱ ይወዳደሩ ነበር፤ ከቁርአኑ ምን ያክሉን እውቀት እንደያዙም ይወያዩና ይጠያየቁ ነበር፤ ምን ያክል ድኩማን ነዳያንን እንደረዱ እና እነዳገለገሉ በመወያየት ነበር የሚያሳልፉት፡፡[5]

ፈጥኖም ሆነ ዘግይቶ የአመራሮች ባህሪና ተግባር በህዝቦቻቸው ዘንድ ከመወረስ አይድንም (የመሪዎች ተግባርና ውሎ ወደ ህዝቦቻቸው መዛመቱና መስረፁ አይቀረም)፡፡ የመሪዎች በጎ ተግባርና ማንነት ማህበረሰብን አዎንታዊ በሆነ መልኩ የመቅረፅ አቅሙ ከፍተኛ ነው፡፡ እንደዚሁም የመሪዎች ዋልጌ ባህሪና አፍራሽ አካሄድ በህዝቦቻቸው ተክለ ቁመና ላይ ያለው አሉታዊ ተፅዕኖ ቀላል አይሆንም፡፡ ለዚህም ነው የአሳ ግማቱ ካናቱ! የሚባለው፡፡

ከቤት አባወራ እስከ ማህበራትና ግዙፍ ድርጅት አስተዳዳሪ ሥራ አስኪያጆች እንዲሁም ከታችኛው እርከን መዋቅር አመራሮችና ፈጻሚዎች እስከ ሀገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለማዊ ተቋማቶችና ግዛት መሪዎች ድረስ ለሚመሯቸው መልካም አርአያ ሆኖ ለመገኘት ከፍተኛውን ትኩረትና ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ስለ ኃላፊነታቸው ጥልቅ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ሸይኽ ኢዳባሊ የተባሉ ምሁር ለአንድ ወደጃቸው “የከፍተኛው መደብ አካል መሆን የታችኛው መደብ ክፍል ከመሆን የተሻለ ደህንነት ዋስትና ሊሆን እንደማይችል መዘንጋት የለብህም፡፡” ብለውት ነበር፡፡

ዑመር ኢብኑ ኸጧብ (ረ.ዐ) አንድን ባህሪ በህዝቦቻቸው ዘንድ እንዳይስተዋል እቀባ ሲያደርጉ እቀባውን የሚጀምሩትና ተግባራዊ የሚያደርጉት መጀመሪያ በቤተሰባቸው ነበር፡፡ ቤተሰቦቻቸው እንዲሰባሰቡ ካደረጉ በኋላ “በህዝቦቼ ላይ ይህንና ያንን እንዳይተገብሩ እቀባ አድርጌያለሁ፤ ንስር አሞራ ስጋን ፍለጋ ከሩቁ እንደሚቃኝ ሁሉ እናንተንም እንዲሁ ህዝቦቼ ይከታተሏችኋል፡፡ እናንተ ለዚህ እቀባና መመሪያ የማታድሩ ከሆነ እነርሱም የእናንተን እግር ይከተላሉ፡፡ በአላህ ይሁንብኝ ከእናንተ አንድኛችሁ ይህን እቀባ ዘንግታችሁ ህግን ብትጥሱ ሌሎች ሰዎችን ከምቀጣው በከፋ ሁኔታ እቀጣዋለሁ፡፡ እናም ለእቀባው የመታዘዝና ያለመታዘዝ ሙብት አላችሁ፡፡”[6] ይሉ ነበር፡፡

ህዝቦች የዜግነት ግደታቸውን ሊወጡ የሚችሉት አመራሩ ኃላፊነቱንና ተልዕኮውን በጥንቃቄና በትጋት ሲወጣ ብቻ ነው፡፡ ታላቁ ሱለይማን (Sulayman The magnificent) በሚባል የሚታወቀው ቱርካዊው ሱልጧን ለአንድ ግዛት አስተዳዳሪ እንዲህ ሲል እንደመከረው ይዘከራል፡-

“ህዝቦችህን ተከታተል፣ ጠብቅ፤ አመራሮች ትክክለኛና የተቀደሱ ከሆኑ ህዝቦቻቸውም የእንርሱን ፈለግ ይከተላሉ፡፡ ህዝቦችህ የአንተ ነፀብራቅ እንጅ ሌላ አይደሉም፡፡ ቀኑን በጾም ሌቱን ደግሞ በስግደትና በዖለት የሚያሳልፉ ሰዎች አሉ ግና የዚህን የዚህችን ምድር ፀጋዎችና ትሩፋቶች እጅጉን የሚያፈቅሩ የኾኑ፤ በዚህ ጊዜ ምድራዊ ፀጋዎች የጣዖትን ደረጃ ይይዛሉ ሰዎችም የፀጋ ጣዖቶችን ያመልካሉ፡፡ እንደ ምድራዊ ፀጋዎች ፍቅር አመራርን የሚያዛባ የሚያጨነግፉ ነገር ከቶም የለም፡፡ ሀብትና ንብረት ለማጠራቀም በፍጹም አታዘንብል፤ ይልቁንም በእጅችህ ያሉ ንብረቶችን ለህዝቦችህ በቅንነት ችራቸው፤ ውሥጥህ ምቀኝነትን እንዲያበቅል ፈቃድህ አይሁን፡፡” የሚል ነበር ምክሩ፡፡

---

[5] Ahmet Cevdet Pasa, Kisas-1 Enbiya ve Tevarih-I Hulefa, Istanbul,1976,I,717; Tabari, Tarikh al-Umam wal-Muluk, Cairo 1939, V, 266-267.

[6] ኢብነል ጀውዚ፣ አል-መናቁብ፣ ገጽ 266

የአላህ መልዕክተኛው (ሡ.ዐ.ወ) አቋም እና ድርጊቶቻቸው ለአመራርነት ሁነኛ ተምሳሌት ናቸው፡፡ ለባልደረቦቻቸው እና እነርሱን ለሚያጋጥሟቸው እንቅፋቶች ቅርብ ክትትልና ትኩረት ነበራቸው፤ ሁልጊዜም የጭንቅ ሁኔታዎችን ገፈት ቀማሽ ነበሩ፤ ጀግናውና ዝነኛው ዓሊይ (ረ.ዐ) እንኳን በአደገኛና በአስጨናቂ ፈታኝ ወቅት በነብዩ ጀርባ ይጠለሉ እንደነበር ዘግበዋል፡፡ እናም አመራር ማለት ለሚመሩት ህዝብ ዋጋ በመክፈል ቀድሞ መምራት ነው፡፡ አመራሮች በሚመሩት ጉዳይ ላይ ሰፊ ተሳትፎ ከሌላቸው በትክክል የአመራር አገልግሎታቸውን ሊሠጡ እንደማይችሉ መሪዎች ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

በርቀትና አድካሚ በሆነ ጉዞ ወቅት የአላህ መልዕክተኛው (ሡ.ዐ.ወ) በጉዞ የደከሙ ባልደረቦቻቸው ጋር አብሮ በመጓዝ ጉልበትና ወኔ ለመሆን አብረው ይጓዙ ነበር፡፡ ሩህሩህ እረኛ የታመመች በጉን ከጀርባው ጥሎ አይጓዝም፤ በክንዶቹ ታቅፏት ቢሆን እንጅ!

የህብረተሰብ መሪዎች ከሞልቃቃነት የፀዱ ሊሆኑ ግድ ይላል፡፡ የአላህ ባሪያዎችና አገልጋዮች መሆናቸውን መቼውንም ሊዘነጉት አይገባም፤ አመራሮች የ”ካሽር” ሥራ ሊሰሩ ይገባል፤ ለእነርሱ የማይገባቸውንም ጥቅም ለሚገባቸው ሊያሰራጩ ይገባል፤ በአምላካዊው ችሎት ፊት አንድ ቀን ቆመው በአመራርነት ስለተሸከሙት ኃላፊነት አንድ ቀን መጠየቃቸውና መመርመራቸው አይቀርምና!

ኢማም ማሊክ በእርሳቸው ዘመን ለነበረው ኸሊፋ የጻፉት ተግሳጻዊ ደብዳቤ የሚከተለው ነበር፡-

*«እኔ እስከማውቀው ድረስ ዑመር (ረ.ዐ) የሀጅ ጉዞ ለአስር ጊዜ ማድረጋቸውን አውቃለሁ፤ ግና ለእያዳንዱ የሀጅ ጉዞ የሚያውሉት የገንዘብ መጠን 12 ዲናሮችን ብቻ ነበር፡፡ በዛፍ ጥላ ስር እንጅ ለንጉስ በተጣለ ድንኳን ውሥጥ አይተኙም ነበር፤ የውሃ ወይም የወተት መያዣ እርኮታቸውን[7] በትከሻቸው ይሸከሙ ነበር፡፡ የነዳያንን ችግር ለይቶና ተረድቶ መፍትሄ ለመስጠት በተቸገሩ ሰዎች ዙሪያ ያንዣብቡ ነበር፤ ዑመር ጥቃት በደረሰባቸውና በተጎዱ ወቅት ባልደረቦቻቸው ዑመርን ለመመልከትና ለማመስገን ሽሚያ ነበራቸው፤ ይህን ያስተዋሉት ዑመር በዚያ ስቃይ ውስጥ ሆነው ሳለ ተሻሚዎቹን እንዲህ አሏቸው፡-“ከወርቅ የተሰራች ዓለም ብትኖረኝ ኖሮ የመጨረሻውን የፍርድ ችሎት ፍርሃትና ስጋት ለመላቀቅ ስል በነጻ አሳልፌ እሰጣት ነበር፤ ይህ አይነቱ ምስጋና ያለጥርጥር ማተለያ መሆኑን ጠንቅቄ እረዳለሁና!”»*

የኢማም ማሊክ ደብዳቤ ቀጥሏል፡- *“ ዑመር (ረ.ዐ) ሁልጊዜ ፍትሃዊ ድርጊቶችን ያደርጉ ነበር፤ የአላህ መልዕክተኛው (ሡ.ዐ.ወ) ለዑመር ከጀነት ነዋሪዎች መካከል እንዱ እንደሆኑ ብስራት ነግረዋቸዋል፤ ግና ዑመር በዚህ ድንቅ ብስራት አልተዘናጉም ነበር፤ የሙስሊሙን ዑማ ጉዳዮች ለማቃናት ሲሉ ራሳቸውን የህዝብና የኃላፊነት ሎሌ አድርገው ኖረዋል፡፡እንደ አንተ አይነት አመራሮች የዑመርን (ረ.አ) እሳቤ ሊቀዳጁና ሊጋሩ ይገባል፡፡*

ስፔንን የተቆጣጠራትን የጧሪቅ ኢብን ዘይድ የተገራና የተጣጣመ ማንነትም ሁነኛ አርአያ ነው፡፡ ከ90 ሺህ በላይ የጠላት ጦርን በ5 ሺህ ወታደር ድል የነሳ ጀግና ነው፡፡ ጦርነቱን በድል አጠናቅቆ በስፔኑ ንጉስ ሀብትና ካዝና መካከል ሲጓዝ ለራሱ እንዲህ እያለ ይራመድ ነበር፡ *“ አንተ ጧሪቅ ሆይ! ትላንት አንገቶችህ በጠፈር የተለጎሙ ባሪያ ነበርክ፤ አንድ ቀን አላህ አርነቱን አጎናጸፈህ፤ ከዚያም የጦር አዛዥ (ኮማንደር) የመሆን እድሉን አገኘህ፤ ዛሬ እንሆ ስፔንን ተቆጣጥረሃል! በስፔን ንጉስ ቤተ-መንግስት ውሥጥ እንሆ ትገኛለህ፤ ተጠንቀቅ! ነገ አላህ ፊት እንደምትቆም አትዘንጋ!”* ይል ነበር፡፡

---

[7] ከቆዳ በተለይም ከግለገል በግ ወይም ፍየል ቆዳ የተሰራች የውሃ መያዣ

የአመራርንና የማስፈጸም ኃላፊነትን የተሸከሙ ህዝብ አገልጋዮች በራሳቸው ላይ የአገልጋይነት ስሜት ሊያዳብሩ ይገባል፤ የህብረተሰባቸውን ጉዳዮች ለመከወን የተቀጠሩ የህዝብ አገልጋዮች መሆናችን ሊያምኑ ይገባል፤ ሙሳ አፈንዲ የተሰኙ ቀደምት አባት እንዲህ ማለታቸው ተዘግቧል፡ የህዝብ መሪዎች እንደ ህዝብ አገልጋይነታቸው ህዝቦቻቸውን በእዝነት፣ በፍቅርና ቅንነት መንከባከብ ይኖርባቸዋል፤ በተቆናጠጡት ዙፋን ሳቢያ ይኮሩ ዘንድ እርስ በእረሳቸውም ሊፈቃቀዱ አይገባም፡፡ "እነዚያ በሀይማኖት ጉዳይ ላይ ህዝቦችን የሚያገለግሉ በሀይማኖት ማገልገል እድል ከፈጣሪ የተገኘ ቡራኬ መሆኑን ሊረዱ ይገባል፡፡ ምክንያቱም በርካቶች የዚህ እድል ባለቤት ወይም ተጠቃሚ አይደሉምና፡፡ ሀይማኖትን ሊያገለግሉ የሚያስችሉ አያሌ ብቃት የተላበሱ በርካታ ሰዎች አሉ፤ ግና በተለያዩ ምክንያቶች ለምሳሌ በጊዜና በቦታ ማነቆዎች ሳቢያ ይህን እድል መጠቀም አልቻሉም፤ ስለዚህም አገልጋዮች ለሚያገለግሏቸው ምስጋናን ሊቸሩ ይገባል፡፡ ምክንያቱም ተገልጋዮች የማገልገልን እድል አስገኝተውላቸዋልና፡፡"

መሪዎች በማህበረሰባዊ ጉዳዮች ላይ ሐይማኖታዊ ግንዛቤ ባላቸው ወቅት ያ ማህበረሰብ በቁሳዊውም ሆነ በመንፈሳዊ ውሎው መሻሻል ያሳያል፡፡ አመራሩ ይህን ሁለንተናዊ መሻሻልን መቀዳጀት የሚሻ ከሆነ ጥበበኛ ሰዎችን፣ ምሁራንና የሰከኑ አማካሪዎችን ማሳተፍና በነርሱም መታገዝ ይኖርባቸዋል፡፡ አመራሮች ከንቱ አወዳሾች ህሌናቸውን እንዲያጨልሙባቸው መፍቀድ አይኖርባቸውም፡፡ የህዝብን ተጨባጭና ግኝ ማነቆዎችን ለይተውና ጥናት አድርገው የሚያቀርቡና መሬት ላይ የሚወርድ መፍትሔ ማመንጨትና የመፍትሄው አካል ሊሆኑ የሚችሉ ብልህ አማካሪዎችን ሊይዙ ይገባል፡፡ ከበቂና አቅም ካላቸው ብልሃተኛ፣ አስተዋይ አማካሪዎች ጋር መመካከር የነቢያት ፈለግ ነውና፡፡ ምንም እንኳን ቅሉ የአላህ መልዕክተኛ ቢሆኑም ነቢዩ ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) የእውቀትባለቤቶችን ያማክሩ ነበር፤ ይህን ፈለግ ነው የተውሉን፡፡

ሠላማዊ እና የተረጋጋ ማህበረሰብን ለመፍጠር አመራሩ ፍትሃዊና ቅን እስከሆነ ድረስ ተመሪዎች ለአመራሩ ተገዥና ለህግጋቱ አዳሪ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ይህ ሲባል ግን ህዝቦች አመራሮቻቸውን ሊቆጣጠሩ ግድ ይላል፤ መሪዎች በስነ-ምግባር ላሽቀው፣ ኃላፊነትን ለመወጣት የማይችሉ በሆኑ ጊዜ ህዝቡ ሊያስጠነቅቃቸው ይገባል፡፡

ዑመር (ረ.ዐ) ኸሊፋ በሆኑ ጊዜ ህዝቦቻቸውን እንዲህ ሲሉ ጠየቋቸው፡ " ህዝቦቼ ሆይ! በፍትህ ባለስተዳድራችሁ ምን ታደረጉኛላችሁ?" ብለው ጠየቁ፤ አንዱ ታዳሚ እንዲህ ሲል መለሰ፡ " ዑመር ሆይ! አንተ ከቀጥተኛው መንገድ ብትርቀና ፍትህን ብታጓድል በሰይፋችን ወደ ቀጥተኛው ፍኖት እናመጣሃለን፡፡" አለ፡፡ በዚህ ጊዜ ዑመር " አላህ የተመሰገነ ይሁን! ፈር ለቅቄ ብሄድ የሚያቅቡኝና ወደቀጥተኛው መንገድ የሚመሩኝ ጓደኞች አሉኝ፡፡" አሉ፡፡

ዑመር (ረ.ዐ) በሌላ ወቅትም እንዲሁ እንዲብ ማለታቸው ተዘግቧል፡- " እጅጉን አድርጌ የምወደው ሰው ማለት ስህተቶቼን የሚነግረኝ ነው፡፡" ብለዋል፡፡[8]

ህዝብ የሚነግራቸውን፣ የሚተችባቸውን ስህተቶቻቸውንና ውድቀታቸውን ከመናቅ ይልቅ አመራሮች ለህዝብ ግሳፄ እና ትችት ክፍት ሊሆኑ ይገባል፤ ራሳቸውን እንደገና ለማደራጀትና በተሻለ ሁኔታ ለማብቃትም ትችቶቹን እንደ ግብአት ሊጠቀሙባቸው ይገባል፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ ተራ የማህበረሰቡ አካል የሆኑ ግለሰቦች ለአላህ ሲሉ አመራሩን በቅንነት ሊገስጹ ይገባል፤ ለሁሉም ጥቅም ሲባልም መስዋዕትነትም ሊከፍሉ ይከጀላል፡፡ ኃላፊነት በትቂት የአመራሩ ክፍል ጫንቃ ላይ ብቻ የሚወድቅ ሳይሆን የህብረተሰቡን የገነቡት የሁሉም ግለሰቦች ሸክም ነው፡፡

---

[8] አል ሱዩጢ፣ ታሪኽ አል ኹለፋ ገጽ 130

የአመራሮችን ስህተቶች መታገስ እንጅ የአመራሩን መከሸፍ እያስተዋለ ዝምታን መምረጥ የገዘፈ ስህተት ነው፡፡ የአንባገነን መሪዎችን ግፍና ኢ-ፍትሀዊነት ማጽደቅና መደገፍ ታሪካዊና የከፋ ስህተት መፈፀም ነው፡፡ አንባገነንና ጨቋኝ መሪዎችን መከተልና መደገፍ በዚያኛው ዓለምም የእንርሱ ጀሌ ሆኖ መቀስቀስ ማለት ነው፡፡እናም ሁሉም የማህበረሰቡ አካል ማንን እንደሚከተል ጠንቅቆ ሊረዳና የሚከተለውን ሊለይ ይገባዋል፡፡

***«ሰዎችን ሁሉ በመሪያቸው የምንጠራበትን ቀን (አስታውስ)፡፡ መጽሐፉንም በቀኙ የተሰጠ ሰው እነዚያ መጽሐፋቸውን ያነባሉ፡፡ በተምር ፍሬ ሰንጥቅ ላይ ያለውን ክር ያክል እንኳ አይበደሉም፡፡» (ኢስራዕ፡71)***

የአመራሩን ስህተትና ጥፋቶች የማረም የመገሰፅ አልፎም አመራሩን ወደ ቀጥተኛው ፍኖት እንዲመጣ የማድረግ ሥርዓት የአማኝ ማህበረሰብ መገለጫ ኃላፊነት ነው፡፡አቡ ዩሱፍ የተሰኙት ታላቁ ምሁር በታክስና ግብር ላይ በጻፉት ኪታብ- አል ኻረጅ በተሰኘው መጽሀፋቸው የወቅቱን ኸሊፋ ሐሩን አል-ሩሽድን እንዲህ ሲሉ ምክር ጽፈውለታል፡

*"አላህ በሰጠህ ሉዓላዊነት ድባብና ከባቢ ውሥጥ ፍትህን ለማስፈን ትጋትህና ፍላጎትን መቼውም አትጣ፤ በአላህ ፊት፣ በፍርዱ ቀን እጅጉን ደስተኛው እረኛ ማለት መንጋዎቹ በእርሱ የረኩበት ነው፡፡ በጥመትና በአንባገነንነት አላህ በመካድ አትጥፋ ህዝቦችህም የአንተኑ አቅጣጫ ተከትለው ይጠፋሉና፡፡በብስጭት አትፍረድ፣ በትዕቢትና በእብሪትም ትዕዛዝ ኢታውርድ፤ የዚህችን ዓለምና ደስታና የቀጣዩን ዓለም ደስታ በመምረጥ ላይ አጣብቂኝ ውሥጥ ከገባህ የቀጣዩን ዓለም መልካም ምረጥ፡፡ የዚህችን ዓለም ቅጽበታዊነትና የቀጣዩን ዓለም ዝንተ ዓለማዊነት እንዳትረሳ፡፡"*[9]

ህዝቦች የመሪዎቻቸውን ዝንባሌ ባህሪ የሚወርሱ እና የሚቀዱ በመሆናቸው፤ አመራሮች ደግሞ ዝንባሌዎቻቸውንና ባህሪዎቻቸውን የሚፈጥሩትና የሚያላምዱት በህዝቦቻቸው ልክ በመሆኑ እያንዳንዱ የማህበረሰቡ አባል ግለሰብና የአስተዳደሩ አመራር አባል በቀጥተኛውና በፍትሃዊ ፍኖት ላይ መጽናትና መገኘት ይኖርበታል፡፡የአንድ መካኒክ ክህሎት የሚለካው በሚጠግነው ማሽን ሁኔታ ሲሆን ማህበረሰብም ልክ እንደ ማሽን ነው፡፡ አስተዳደሩና አመራሩ ደግሞ እንደ መካኒኩ ናቸው፡፡ በአንድ ማኅበረሰብ ውሥጥ ያሉ ሁነቶች በተደጋጋሚ የሚበላሹ ከሆነና በሽታቸውም የሚጸና ከሆነ አመራሩ ራሱን ተጠያቂ ሊያደረግ ይገባዋል፡፡ ይህ ተጠያቂነት ደግሞ ለከፍተኛው አመራር ብቻ የሚገደብ ሳይሆን በተዋረድ የታችኛው እርከን አመራርም የድርሻውን ቀርሶ ተጠያቂነቱን ሊወስድ ይገባዋል፡፡ መሪዎች ህዝቦቻቸው እና የበታች አመራሮቻቸው እንዲሁም ፈጻሚዎቻቸው በአስተዳደር ግዛታቸው ውሥጥ ስለሚፈጽሙት ነውረኛ ተግባርና ስለሚተላለፏቸው የሕግ ጥሰቶች ንቁ ሊሆኑ ይገባቸዋል፡፡

በእርግጥ በአስተዳደሩና በአመራሩ ሁለንተና ፍፁም የረካና በተሟላ ደስታ የናኘ ግለሰብ ማግኘት ያስቸግራል፤ ይህም የሰው ልጅ የሰዎችን ጉድለቶችና ህፀፆች ለጥጦና አጉልቶ በመተቸት ላይ የመጠመድ ባህሪ ስላለው ነው፡፡ይሁን እንጅ ተመሪዎች ሆንም መሪዎች የየራሳችን ጉድለቶች እና ክፍተቶች ለይተን ራሳችንን መገምገም ይኖርብናል፡፡ መልካም ስብዕናን የተላበሱ የማኅበረሰብ አባላትን ቁጥር ከፍ ባደረግን ጊዜ በቁሳዊውም ሆነ በመንፈሳዊው አውድ ሁለንተናዊ መሻሻልን እንቀዳጃለን፤ ይህም በአላህ ፈቃድ የበቁና ኃላፊነታቸውን የሚወጡ ቅንና ቆራጥ አመራሮችን ወደ ስልጣን የማምጣት እድላችንን ያሰፋልናል፡፡ ስለዚህም አመራሩ በመሚሩት ህዝብ ወይም ማኅበረሰብ ማንነት መደሰት ካልቻሉ ራሳቸውን አጥብቀው

---

[9] አቡ ዩሱፍ፣ ኪታብ አል ኻረጅ፣ ገጽ3-4

መመርመርና መጠየቅ ይኖርባቸዋል፤ ህዝቦቻቸውን መክሰስና መውቀስን ትተው ራሳቸውን ለማሻሻል መጣር ይኖርባቸዋል፡፡

በኮሶቫ ዘመቻ የተሰዋውና የኡስማንያ (ኦቶማን) ሱልጧን የነበረው ሙራድ ፲ኛ መንፈሳዊና ቁሳዊ ምጥቀትን አጣምሮ የያዘ ልቦና ባለቤት ነበር፤ መጀመሪያ ራስን ተጠያቂ የማድረግ ተምሳሌትን አስቀምጦልናል፤ በኮሶቫ ዘመቻ ወቅት ግድያው የተፋፋመበት፣ በሙብረቃማው የዓየር ንብረት ጭጋግ ውሥጥ ዓይኖች ምልከታቸው ባጠረበት፤ አለመረጋጋት፣ ሁካታና መደበላለቁ በበዛበት ሁኔታ ውሥጥ ሆኖ ጦሩ ሲፍረከረክ በተመለከተ ጊዜ ሙራድ ሁለት ረከዓ ሶላት ለፈጣሪው በመስገድ እንዲህ ሲል ዱዓ አደረገ "ፈጣሪዮ ሆይ!" አለ በእንባ እየታጠበ "ፈጣሪዮ ሆይ! ይህ ሙብረቃማ የአየር ሁኔታ የተፈጠረው በኔ ወንጀል ከሆነ እባክህ እነዚህን ሀጢያት አልባ ወታደሮች በእኔ ኀጢያት ሳቢያ አትቅጣቸው! የውድቀታቸውና የሞታቸው ምክንያት እኔ አልሁን!" በማለት አልቅሶ ዱዓ አደረገ፡፡ ወዲያውም ሙብረቁና ብልጭታው ቆመ፤ ወታደሮቹም ጠላቶቻቸውን ድል ነሱ፡፡ትልቅም ድል ሆነ፡፡ ሙራድ በዘመቻው የተጎዱና የተሰውትን መጎብኘትና መፈለግ ጀመረ፤ግና ቢዚህ ወቅት በአንድ በቆሰለ የሰርቢያ ወታደር ተወግቶ ለሞት ተዳረገ፡፡

ማኅበረሰብ የሚራመደውና የሚያድገው በአላህ ፈቃድ ሁላችንም ራሳችንን ተጠያቂ ስናደርግና መሻሻል ስናመጣ ነው፡፡ ይህን መርህ ለማረጋገጥ በርግጥ ትቂት ያልተለመዱ ሁኔታዎች ይኖራሉ፡፡ ለምሳሌ ህዝቦች በንቅዘትና በክህደት ጥፋት በጠፉ ጊዜ አላህ ነቢያቶችንና መልዕክተኞችን ለዚያ ማኅበረሰብ አብዮተኛ አድርጎ ለተሀድሶ ይልካቸዋል፤ ለዚህም ነው የአላህ መልዕክተኛው ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) እንስት ጨቅላዎቻቸውን ከነህይዎታቸው አፈር የሚያለብሱ፣ በከፊል የውሬነት ጠባይ ያደረባቸው፣ እዝነት አልባ ጣዖት አምላኪ ህዝቦችን ከነበሩበት ድቅድቅ የጃሂሊያ ጽልመት ወደ ብርሃናማው ጎዳና ለማሻጋር የተላኩት፡፡ ይህ በአርግጥ የአላህ ቡራኬና ጸጋ ነው፡፡ ቅድመ ኢስላሙን የአረብ ማኅበረሰብ ተክለ ቁመና በማጥናት ከላይ የጠቀሰነው በስነ-ምግባር ከበቁ ህዝቦች ትክክለኛና ቆራጥ መሪዎች ይወለዳሉ የሚለው መርህ ሊሰራ እንደማይችል እንረዳለን፡፡ ይህ የአላህ ጣልቃ ገብነትና ይሁን ባይነት ላይ የተመሰረተ ክስተት ብቻ ነውና፡፡ የፈጣሪ ህግጋት፣ ሥርዓትና ቱኑፋቶች መከሰትና እውን ከመሆናቸው ጀርባ የአላህ ፈቃድና ችሮታ እንጅ ሌላ አይደለም፡፡

ይህ ዓይነቱ መለኮታዊ ፈቃድና እዝነት ከዚህ በኋላ እውን ይሆናል ብለን ልንጠብቅ አንችልም፤ የነቢያቱ መቀምቀሚያና መጨረሻ የሆኑት መልዕክተኛው ነቢዩ ሙሐመድ (ሠ.ዐ.ወ) ከተላኩ በኋላ መጸኢ ነቢይ አይኖርምና፤ መልዕክተኞችን የመላክ በር ተከርችሟልና፡፡ አሁን በሰው ልጆች እጅ ያለው እድል ህዝቦች ራሳቸውን በዲንና በመንፈሳዊ እድገታቸው የማሻሻል ተልዕኮ ብቻ ነው፡፡

ራሳችንን በዲን ለማሻሻል፣ በመንፈሳዊ ገጽታችን መሻሻልን ለማሳየት አያሌ እድሎች አሉን፡፡ ከነዚህ እድሎችና አቅሞች መካከል የመጀመሪያው ተቋማቶቻችንን ለትምህርት፣ ጥናትና ምርምር ክፍት በማድረግና የወደፊት መሪዎችን ለማፍራት በስልጠና፣ በምርምርና በትምህርት ትውልድን የሚያበቁ ተቋማትን ማበራከትና የአቅም ግንባታ ሥራን ማጠናከር ነው፡፡ "በግዙፍ ህዝቦች፣ ጠንካራ አገራት እና በጥገኛ አገራት መካከል ያለው አቢይ ልዩነት በቅጡ በተማሩና በበቁ ምሁራንና ክምችቶቻቸው ላይ ነው፡፡" እንደሚባለው ሁሉ የአንድን ማኅበረሰብ ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶች ማርካት የሚችሉ የተማሩ በርካታ ዜጎች ሊኖሩን ይገባል፡፡ በቅጡ በተማሩና በእውቀት በደረጁ ክፍሎች ብቻ ነው ከሽብርና ሁከት የጸዳ የተረጋጋና ፍትሃዊ ማኅበረሰብ ማስገኘት የሚቻለው፡፡

የሰው ልጆች ማንነት የሚቀረጸው፣ የአኗኗር ዑደታቸው የሚሽከረከረው፣ ዝንባሌያቸውና ተክለቁመናቸው የሚያጠነጥነው እንደ ተምሳሌትና አርአያ አድርገው በሚከተሏቸው ስብዕናዎች ማንነት ላይ ነው፡፡ ህዝቦችን በጽሞናና በበቃ ሁኔታ መምራት የሚችሉቱ የበሰለ ስብዕናና የመጠቀ ግብረገብነት ባለቤቶች ብቻ ናቸው፡፡ ታላቅ ህዝቦችን መቅረጽና እውን ማድረግ የሚችለው ታላቅ መሪ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ተቃዳሚውና አንገብጋቢው ጉዳይ የነገ አመራሮችን በእውቀትና ክህሎት ማብቃት ሊሆን ይገባዋል፡፡ ቱርካዊው ገጣሚ ኒኪፐ ፈዚል ይህንን አስመልክቶ " በቆልት የሌላው ዛፍ የሞተ እንጨት ብቻ ነው፡፡" ይል ነበር፡፡ አንድ የአላህ ባሪያ ደግሞ እንዲህ ማለታቸው ተወስቷል "ለወደድካት ውለድላት!" ይላሉ፡፡ ህዝብህን የምትወድ ከሆነ የነገ መሪ ቅረጽለት ማለታቸው ነው፡[10]፡

ሙስሊሙ ዑማህ ታሪኩን ጠንቅቆ የሚረዳ ዑማውን ለማገልገል ዝግጁነት ያለው በኢማኑ ያደገና የበቃ ትውልድን ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ ይህ ካልሆነ አላህ (ሡ.ወ) ህዝቦች የነበሯቸውን ጸጋዎችና በጎ ስልጣኔዎች፣ እዲሁም ትሩፋቶችን የሚያነሳበት መርህ አለው፡፡ የቀደምት ህዝቦችና ስልጣኔዎች የታሪክ ገፆችም የሚያሳብቁትና የሚመሰክሩት ይህንኑ ነው፡፡

በመጀመሪያ አላህንና የአላህ መልዕክተኛውን ፍቅርና መከተል በልባችን ውስጥ ካሳደርን አላህንና መልዕክተኛውን የሚከተሉ ትውልዶችን፣ ለዑማው መሰዋዕት ለመሆን ዝግጁነት ያላቸው ተተኪ ትውልዶችን ለማብቃትና ለመቅረጽ ይቻለናል፡፡ እውነተኛና ተጨባጭ ኢስላማዊ ማንነትን የሚያንጸባርቁ ሙስሊም ማኅበረሰብን መትከል የሚቻለውም በዚህ መርህ ብቻ ነው፡፡

አላህ (ሡ.ወ) ቅን፣ኃላፊነትን መሸከምና መወጣት የሚችሉ፣ ሥራቸውንና ተልዕኳቸውን ጠንቀቅው የሚረዱ፣ ባለ አንጸባራቂ ስብዕና ባለቤት የኾኑ አመራሮችን ከከፍተኛ እስከ ዝቅተኛው እርከን ይሰጠን ዘንድ አላህን እንማጸናለን፡፡ በሁሉም የዓለማችን አፅናፍ ህዝባችንን የሚያገለግሉ፤ በቁሳዊውና በመንፈሳዊ እድገት እምርታዊ ለውጥ ማምጣት የሚችሉ፣ ዑማውን ወደ ተሻለ ተክለ ቁመና የሚያሸጋግሩ በሳል በኢማናቸው የበቁ ትውልዶችን እናስገኝ ዘንድ የአላህ እርዳታ እንዲሆን አላህን እንማጸናለን፡፡

አሚን

---

10 ተርጓሚው